**ደንብ ቁጥር 181/2008**

# የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የመኖሪያ ቤት ግንባታ ማኅበር አደረጃጀትን ለመወሰን የወጣ ደንብ

የመኖሪያ ቤት ችግር ለመፍታት መንግስት ያወጣውን ፖሊሲና ስትራቴጂ ወደ ሥራ በመቀየር በኦሮሚያ ክልል ከተሞች ወስጥ የሚታየውን የመኖሪያ ቤቶች ችግሮች ለመፍታት አሠራሩንማዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በማኘቱ፤

የመኖሪያ ቤቶች ፕሮግራም ወስጥ አንዱ የሆነውን ለማበከር ዜጎች እንደየፍላጎታቸው ተደራጅተው በመኖሪያ ቤት ግንባታ ማኅበር ፕሮግራም በማቀፍ መኖሪያ ቤት ማንባት እንዲችሉ ለማድረግ ሁኔታን ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በማኘቱ፤

በአዋጅ ቁጥር 163/2003 አንቀጽ 65(2) እና በፌዴራል የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ59 መሠረት የሚከተለው ደንብ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥትየመኖሪያ ቤት ግንባታ ማኅበር አደረጃጀት ደንብ

ቁጥር 181/2008 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ወስጥ፡-

1) "**መንግስት**" ማለት የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ነው፡፡
2) "**ክልል**"ማለት የኦሮሚያ ክልል ነው፡፡
3) "**ቢሮ**" ማለት የኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ነው፡፡
4) "**አዋጅ**" ማለት የፌደራል ኅብረት ሥራ ማኅበር አዋጅ ቁጥር 147/1991ማለት ነው፡፡
5) "**ጽህፈት ቤት**" ማለት የዞን ወይም የወረዳ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጽህፈት ቤት ማለት ነው፡፡
6) "**የከተማማስተዳደር**"ማለት የራሳቸው ምክር ቤት ያላቸው የኦሮሚያ ክልል ከተሞች ማለት ነው፡፡
7) "**ኤጀንሲ**" ማለት የኦሮሚያ ክልል መንግስትየከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ ማለትነው፡፡
8) "**ዩንዩን**"ማለትተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑመሠረታዊየመኖሪያ ቤት ግንባታ ማኅበራት አብረውየተደራጁበት የሁለተኛ ደረጃ ማኅበር ማለት ነው፡፡
9) "**የሊዝ መነሻ ዋጋ**" ማለት ትላልቅ የመሠረተ ልማቶችንለማዘርጋትየሚያስፈልገውን ወጪ በሜሬቱ ላይ ሰፍሮ የሚገኘውን ንብረት ለማስነሳት እና ሌሎች ወጪዎችን ከግምት ወስጥ ያስገባ የሜሬት መነሻ ዋጋ ማለት ነው፡፡
10) "**ማኅበር**"ማለትለመኖሪያቤትግንባታተደራጅቶና ተመዝግቦሕጋዊሰውነትያገኘ ማህበርማለትነው፡፡

11) **"ነባር ማኅበር"**ማለት ከ2001 ዓ.ም በፊትለመኖሪያ ቤት ግንባታ ተደረጅቶየተመዘገበና ሕጋዊ ሰውነት ያገኘማህበር ማለት ነው፡፡

12) **"አዲስ ማኅበር"** ማለት በኦሮሚያ እንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ በወጣው መመሪያ ቁጥር 11/2007እና ይህ ደንብ ከወጣ በኋላለመኖሪያ ቤት ግንባታ ተደራጅቶ የተመዘገበና ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠውማኅበር ማለት ነው፡፡

13) **"መሥሪያ ቤት"**ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም የግል ድርጅቶች ለሠራተኞቻቸው የመኖሪያ ቤት ግንባታ ወጪ በከፊል ወይም በሙሉ ከፍሎ መኖሪያ ቤታቸውንለማንባት ፈቃደኛ የሆነ ማለት ነው፡፡

14) **"ዲያስፖራ"**ማለት የኢትዮጵያ ዜጎች ሆነው ከኦሮሚያ ክልል ሄደው ውጭ ሀገር እየኖሩ ያሉ ማለት ነው፡፡

15) **"የተመለሰዲያስፖራ"** ማለትየኦሮሚያ ክልል ነዋሪ ሆኖ ውጭ ሀገር ቆይቶ ወደ ሀገር ከተመለሰ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ የቆየ ማለት ነው፡፡

16) **"የከተማ ቤት"** ማለት ባለ አንድ ፎቅ(G+1)፣ ሁለት ፎቅ(G+2)፣ ሦስት ፎቅ(G+3) ቤት ሆኖ ራሱን የቻለ መግቢያና መውጫ በር ያለውግቢ ማለት ነው፡፡

17) **"አፓርታማ"** ማለትባለ አራት ፎቅ(G+4) ቤትና ከዚያ በላይ ሆኖ በተፈቀደው የሜሬት አጠቃቀም ፕላን መሠረትንብረትነቱ የእያንዳንዱ የማኅበሩ አባል ወይም የግል የሆነ የጋራ ቤት ማለት ነው፡፡

18) **"ቪላ"** ማለት በከተማው የቦታ ምደባ ፕላን መሠረት በብሎኬት፣ በድንጋይ ወይም በአካባቢ ማሳሪያ የተገነባ ቤት ራሱን የቻለ ግቢ ያለው ማለት ነው፡፡

19) **"ለቤት ግንባታ የሚውል የአከባቢ ማሳሪያ"**ማለት በከተማውየቦታ ምደባ ፕላንመሠረት የማኅበሩን አቅም ማዕከል አድርጎ በከተማው አስተዳደር ወሳኔ ለመኖሪያ ቤት ግንባት የሚውል መሣሪያ ማለት ነው፡፡

20) **"ዝግ ሒሳብ"**ማለትለቤቶች ግንባታ ማነበር በማኅበሩ ስም ለቤታቸው ግንባታ የሚውል ወጪ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ በኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ማህበር ባንክ ወይም በኦሮሚያ ብድርና ቁጠብ ማህበር ወስጥ የሚቀመጥየሚንቀሳቀስ ሒሳብ ማለት ነው፡፡

21) **"ዲዛይን"** ማለትየአንድ ህንፃና ከዝያ በላይ ማጠን ዓይነትና ስፋትእንዲሁም መዛሪያና ዲዛይን የሚያሳይየህንፃ ግንባታ ዘደምሪጃማለት ነው፡፡

22) **"ሰው"**ማለትየተፈጥሮሰው ወይምበሕግየሰውነትመብትየተሰጠው አካልነው፡፡

23) **"የመንግስት ሠራተኛ"**ማለትበመንግስት መሥሪያ ቤት ወይምበመንግስት የልማት ድርጅቶች ወስጥተቀጥረው እየሠሩ ያሉ ሰዎች ማለት ነው፡፡

**3.የፆታአገላለፅ**

በዚህደንብ ወስጥበወንድፆታየተገለፀወሴትንም ይጨምራል፡፡

**4.የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ ህጋዊ ሰውነት ባላቸው የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ሁሉም ከተሞች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የመኖሪያ ቤት ግንባታ ማህበር አባል ሆነዉ ለመደራጀትና ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች፤

## 5. በአዲስ ማህበር ለመደራጀት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

በአዋጁ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (2-5) ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ማህበር አባል ለመሆን ለመደራጀት የሚከተሉት መስፈርቶች በተጨማሪ መሟላት አለባቸው፡፡

1) ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ ሆኖ በህግ ያልታገደ፣
2) በከተማውውስጥ በተከታታይለ2 ዓመትናከዚያበላይእየኖረያለ፣
3) በዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ2ሥርየተደነገገውእንደተጠበቀሆኖየሜትአቅርቦትችግርየሌለባቸውከተሞችየሁለትዓመትቆይታሳይጠበቁለ6 ወርበከተማው ውስጥየኖረውንሰውማደራጀትይቻላል፤ አፈጻጸሙበሚወጣውመመሪያየሚወሰንይሆናል፡፡
4) በክልሉ ከተሞች ውስጥበራሱምሆነ በባለቤቱስምቤትወይምየመኖሪያቤትሜትየሌለወይምኖሮትለሶስተኛወገንያላስተላለፈ፤
5) በዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ2ሥርየተደነገገውእንደተጠበቀሆኖበስራምክንያትከአንድቦታወደሌላቦታየተዛወሩትንአይመለከትም፡ አፈፃፀሙበሚወጣውመመሪያየሚወሰንይሆናል፡፡
6) የቤቶችልማትፕሮግራምበሚካሄድበትከተማውስጥወይምበክልሉመንግሥትበፊንፊኔከተማውስጥበ10/80፣ 20/80 እና40/60 የቤትልማትፕሮግራምእድልያላገኘወይምለማግኘት ያልተመዘገበ ተመዝግቦምከሆነ መሰረዙንየሚገልጽማስረጃየሚያቀርብ፣
7) ቋሚየመኖሪያአድራሻውበከተማውውስጥሆኖለተከታታይሁለትዓመትበከተማውውስጥባይኖርምበቂማስረጃማቅረብየሚችል፣ የአፈፃፀሙሁኔታበሚወጣውመመሪያየሚወሰንይሆናል፡፡
8) በዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ(1-8) ሥርየተደነገገውመስፈርትእንደተጠበቀሆኖነባርማህበርከሆነ፣የሀገርውስጥነዋሪማህበርከሆነካደራጀውአካልየተሰጠውንየህጋዊሰውነትማስረጃማቅረብየሚችልመሆንአለበት፡፡

## 6. አባላት የሚደራጁበት ቦታ

1) የወረዳየመንግስት ሠራተኛ ከሆነ የመንግስት ሰራተኛ በመሆኑ በወረዳ ከተማ ወይም በሚኖርበትአንድ የወረዳ ከተማ ውስጥ ሊደራጅ ይችላል፤
2) በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ባሉ ፋብርካዎች፣ዩኒቨርሲቲዎች ወይም የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ውስጥ የሚሠራ ሠራተኛ ከሆነ በሚኖርበት ከተማ ወይም እየኖረበት ባለዉ የወረዳ ከተማ ውስጥ ሊደራጅ ይችላል፤
3) በኦሮሚያበክልል ደረጃ ባሉ መሥሪያ ቤቶች እና በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠራ ሠራተኛ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ውስጥ ባሉ ከተሞች ወይም እሱ በሚጠው ሌላ አንድ ከተማ ውስጥ ሊደራጅ ይችላል፡፡

## 7. የክፍያሁኔታ

1) የማህበሩአባልበሊዝበሚተዳደር ከተማ ውስጥ በሊዝ መነሻ ዋጋ፤ በኪራይ በሚተዳደር ከተማ ውስጥ የሜት ኪራይ ክፍያ በመክፈል የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ የሚያገኝ ይሆናል፡፡
2) የተቀማጠውን የቤትዋጋ ግምትመሠረት በሚድረግ ለቤት ግንባታ ሲደራጅ 15%፤ ሜቱን ሲረከብ 15% የሚቆጥብ ሆኖ ቀሪውን ክፍያ በቤት ግንባታ ሂደት ውስጥ የሚቆጥብ ይሆናል፡፡

3) ዲያስፖራ ከሆነ ሲደራጅ የቤቱ ግንባታ ውጭ 30%፣ሜቴን ሲረከብ 20% በኢትዮጵያንግድ ባንክ ወይም በኦሮሚያ የህብረት ስራ ማበር ባንክዝግ ሂሳብ በውጭምንዛሪ የሚቆጥብ ሆኖ ቀሪውን ክፍያ በቤት ግንባታ ሂደት ወስጥ የሚቆጥብ ይሆናል፡፡

**8. ለአርሶአደር ወይም ለአርብቶ አደር የሚያስፈልግ ማስፈርት**

አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 ስር ካለው ማስፈርት ወጪ የሚሟሟ ከሆነ በወረዳ ከተማ ወስጥ ሊደራጅ ይችላል፡፡

**9. በአዲስማህበርወስጥ ሜራጀት**

አዲስ በሚደራጅ ማህበር ወስጥ የሚደራጅ ሰው ፍላጎት ያለው እና በገንዘብ አቅም ተመጣጣኝ የሆነ እና አብሮ ለመሥራት የተግባባ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የሜት ስፋት፣የቤቶች አይነት እና የግንባታ ዋጋ

**10.የሜትስፋት**

ለማህበሩ አባላት ለመኖሪያ ቤት ማስሪያ የሚሰጠው የሜት አሰጣጥ የኦሮሚያ ከተሞችን በሊዝ ለማስተዳደር በወጣው ሕግማስረት ሆኖ የሜቱ ስፋት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1) በ1ኛእና 2ኛምድብከተሞችወስጥለአንድአባልየሚሰጠውእስከ 140እስኳር ሜትርሆኖ ግንባታው በከተማው ፕላን ደረጃና ማህበሩ በሚሰጠው የቤት ዓይነት ሁኔታ ይሆናል፡፡
2) በ3ኛ ምድብ ከተሞች ወስጥ ለአንድ አባል እስከ 160 እስኳር ሜትር ይሆናል፡፡
3) በኪራይ በሚተዳደሩ ከተሞች ወስጥ ለአንድ አባል እስከ 200 እስኳር ሜትር ይሆናል፡፡
4) በ1ኛ፣2ኛእና3ኛምድብከተሞችወስጥበማህበርየሚነባቤትአፓርታማከሆነለአንድማህበርእንደማህበሩአ ባላትብዛትየከተማውንፕላንጠብቆየሚወሰንሆኖእስከ700 ስኩዌር ሜትርእናለአንድሰውእስከ 110 እስኳር ሜትርሊሆንይችላል፡፡
5) በዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ1-4 ስር የተደነገገውእንደተጠበቀሆኖለአንድ ማህበርከሚሰጠው ቦታ ወስጥለአረንጓዴቦታ እስከ 30%ሊኖረወይገባል፡፡

**11.የመኖሪያቤትማህበርሜትዝግጅት**

ለመኖሪያቤትማህበርየሚዘጋጅሜትየመኖሪያ ቤት ግንባታ ቦታ በከተማው ፕላንወስጥ በተወሰነዉ ማስረትየሚጸምይሆናል፡፡

**12.በማህበርየሚሰራ የቤትአይነት**

1) በ1ኛእና 2ኛምድብከተሞችወስጥለቦታውበሚቅደዉፕላን ሁኔታአፓርታሜ የከተማቤት፣ እናየብለቱቤትቪላይሆናል፡፡
2) በ3ኛምድብከተሞችወስጥአፓርታሜ የከተማቤት፣ ብለቱቤትቪላናከአከባቢውበማገኝ ዕቃየሚነባበትይሆናል፡፡
3) በማዘጋጃ ቤት ከተሞችናበታዳጊማዘጋጃ ቤት ከተሞችወስጥበብለቱቤትቪላእናበአከባቢውከሚገኙእቃዎችእንዲገነቡሊፈቀድይችላል፡፡
4) በዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ 1 እና 2 ስር የተደነገገውእንደተጠበቀሆኖበከተማዉነባራዊሁኔታበ3ኛምድብወስጥየተደነገገውማስፈርትበ1ኛእና 2ኛምድብ ከተሞችላይምተፈፃሚ ትየሚኖረውሆኖአፈጻጸሙ25%በላይሊሆንአይችልም፡

2) የማህበርአደራጅአካልማስፈርቱምሟላቱንካረጋገጠበኋላበማህበሩ ስም ዝግየባንክሂሳብበኢትዮጵያንግድባንክ፤ በኦሮሚያየህብረትሥራባንክወይምበኦሮሚያብድርናቁጠባማህበርእንዲከፈትያደርጋል፤ ዝርዝሩበሚወጣውመመሪያየሚወሰንይሆናል፡፡

3) ማህበርለሚደራጅትሥልጣንየተሰጠውአካልማስፈርቱንአሟልቶለተማዘገበማህበርየህግሰውነትየምስክርወረቀትበመስጠትሜቴትማግኘትእንዲችሉለኤጀንሲወያስተላልፋል፡፡

## 15. ነባርየመኖሪያቤትግንባታማህበር

ነባርየመኖሪያቤትግንባታማህበር፡ -

1) ከዚህበፊትተመዝግቦየህግሰውነትየምስክርወረቀትያገኘነባርማህበርበዚህደንብወስጥየተቀመጠውንማስፈርትካሟእንደገናበመመዝብሜቴትሊሰጠውይችላል፡፡

2) በዚህደንብየተቀመጠውንማስፈርትየሞሟ አባላቱ የተጓደሉበት ነባርማህበርሥልጣንበተሰጠውአካልከሌላነባርማህበርጋርበመቀላቀልወይምስምመቀየርሳያስፈልግአዲስአባልበሜጨምርእንደገናየሚደራጅይሆናል፡፡

## 16. የማህበራት ቤት ግንባታን የሚያካሄድ አካል

1) የማህበራትመኖሪያቤትግንባታበኦሮሚያክልልየቤቶችግንባታ ልማት ኤጀንሲ ወይም በማህበሩ በኩል ማህበሩ በሚጠው የግል ድርጅት የሚከሄድ ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማህበሩ አባል በራሱ ወይም በሚጠው የግል ድርጅት ቤት ማንባት ይችላል፡፡ አፈፃፀሙ በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

3) በዚህ አንቀፅ ንሑስ አንቀፅ 1 እና 2 መሠረት የሚከሄደዉ የቤት ግንባታ በተሰጠዉ ዲዛይን ወይም የራሱን ዲዛይን አዘጋጅቶ በዞን ወይም በከተማ ኮንስትራክሽን ፅህፈት ቤት ተረጋግጦበተሰጠው ዲዛይን ማሰረት መሆን አለበት፡፡

## 17. የማህበር አባላት ብዛት

1) የነባርማህበር አባላት ብዛት ቀድሞ በተደራጀበት ይሆናል፡፡

2) የአዲስ ማህበር አባላት ብዛት ከ12 እስከ 24 ሆኖ በአፓርታማ ቤቶች ላይ ቁጥሩ ሊጨምር ይችላል፡፡

## 18. በማስሪያ ቤት በኩል እንዲደራጅ የሚደረግ ሰራተኛ

1) በአንድማስሪያቤትወስጥያሉናየሚተዋወቁ ሰራተኞች አንድ ላይ በመሆን ተመሳሳይ የቤት ፍላጎትና አቅማቸው የሚመጣጠን መሆኑን የሚያሳይ ደብዳቤ ከማስሪያ ቤታቸው በማያዝ በሚያደራጅ አካል ዘንድ መደራጀት ይችላሉ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም በተለያዩ ማስሪያ ቤቶች ወስጥ ያሉ ሰራተኞችም አብረው መደራጀት ይችላሉ፡፡

## 19. ለሠራተኞቻቸው የመኖሪያ ቤት በማህበር የሚነቡ ማስሪያ ቤቶች

ለሠራተኞቹ ቤት ሊሰራላቸው ለሚፈልግ መሥሪያ ቤት የሰዎቹን ስምና በዚህ ደንብ ወስጥ የተወሰነውን ክፍያ ማጠን ገቢ ካደረገ መደራጀት ይችላል፡፡ አፈፃፀሙ በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 20. ማህበርን መመዝገብና ማፅደቅ

1) የመኖሪያቤትግንባታማህበርህጋዊሰውነትለማግኘትየመጠረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያደንብ ማዘጋጀት አለበት፡፡ አፈፃፀሙ በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

2) ማንኛውም የመኖሪያ ቤት ግንባታ ማህበር ስልጣን ባለው አካል ዘንድተመዝግቦ መፅደቅ አለበት፡፡

3) እያንዳንዱ ማህበር በሚወጣው የምዝገባ ፕሮግራም መሰረት በሚደራጀው አካል ዘንድ በአካል ቀርቦ መመዝገብና አባላቶቹንም ማስመዝገብ አለበት፡፡

4) የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ስራ ማህበር እያንዳንዱ አባላቱን በሚወጣው የአሻራ አሰጣጥ ፕሮግራም መሰረት ቀርቦ የጣት አሻራ ማስጠት አለበት፡፡

**21. ከአባልነት ማስረዝና የደምፅ አሰጣጥ ሁኔታ**

ከአባልነት የማስረዝና የደምፅ አሰጣጥ ሁኔታ ማህበሩ በሚያወጣው የመተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

**22. ቅድሚያ ተጠቃሚነትን የሚያስገኙ ወሳኔዎች**

ብቻቸውን የተደራጁ የሴቶች ወይም የአካል ጉዳተኞች ማህበራት በምዝገባ ቅደም ተከተል መሰረት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡

## ክፍል አምስት

## የማህበራት አመራር አካላት

**23. የማህበር አመራር አካላት**

የመኖሪያ ቤት ግንባታ ማህበር የሚከተሉት አመራር አካላት ይኖሩታል፡-

1) ጠቅላላጉባኤ፤

2) ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ፤

3) የቁጥጥር ኮሚቴ፡፡

**24. የማህበራት ከፍተኛ አመራር**

የመኖሪያ ቤት ግንባታ ማህበር ከፍተኛ አመራር የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡

**25. የማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር**

የማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር በማህበሩ የወስጥ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

**26. የስራ አስኪያጅ ኮሚቴ ተጠሪነት፣ብዛት እና ስልጣንና ተግባር**

1) የስራአስኪያጅኮሚቴተጠሪነትለአባላትጠቅላላጉባኤይሆናል፡፡

2) የስራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላት ብዛት ከአምስት እስከ ሰባት ሊሆን ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

3) የስራ አስኪያጅ ኮሚቴ የስራ ዘመን ሶስት አመት ሆኖ አንድ አባል በተከታታይ ከሁለት ጊዜ በላይ በድጋሚ መመረጥ አይችልም፡፡

**27. የቁጥጥር ኮሚቴ**

1) ማንኛውምማህበርሶስትሰዎችያሉትየቁጥጥር ኮሚቴ ከጠቅላላ ጉባኤ ወስጥ ይመርጣል፡፡

2) የቁጥጥር ኮሚቴ የስራ ዘመን ሶስት አመት ሲሆን የኮሚቴው ተጠሪነት ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል፡፡

**28. የስራ አስኪያጁ ስልጣንና ተግባር**

ማህበሩ የስራ አስኪያጅ የሚቀጥረው ሆኖ የስራ አስኪያጁ ስልጣንና ተግባር በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

**29. የገንዘብ ኦዲት**

ማንኛውም ማህበር በመተዳደርያ ደንቡ ወስጥ በሚነገገው ሁኔታና ጊዜ የገንዘብ ሂሳብና ንብረት ምርመራ ያደርጋል፡፡ ዝርዝሩ በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ክፍል ስደስት

## የተለያዩ አካላት ስልጣን፣ተግባርና ሃላፊነት

30. በኦሮሚያ ክልልከተሞች ወስጥ የመኖሪያ ቤት ማህበራትን የሚደረጀት የመመዝገብና ህጋዊ ሰውነት የማስጠት ሥልጣን ለቢሮ፣ ለጽህፈት ቤትና ለከተሞችማስተዳደር ተሠጥቷል፡፡

1) የቢሮሥልጣንናተግባር

በሌሎች ህጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡ -

(ሀ) የማህበሩን መመሪያ ማውጣት፣ የማህበሩን አማሰራረት በተማለከተ የማህበሩን ማኑዋል፣ የመተዳደሪያ ደንብ ሞዴልና የማህበሩን የመማስረቻ ፅሁፍ ያዘጋጃል፤

(ለ) ደረጃውን የጠበቀ ዲዛይንና የሚነባውን ህንጻ ቶፖሎጂ እንዲሁም የግንባታ ዋጋ ግምት ያዘጋጃል፤ የሚከታተያ አሠራር ይዘረጋል፤ ሥልጠናና ግንዛቤ ይሰጣል፤ አፈፃፀማቸውን ይገመግሜል፤

(ሐ) ለመኖሪያ ቤት ማህበር በምደባ የሚሰጠው መሬት በወቅቱ ማዘጋጀቱን ያረጋግጣል፤ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

(መ) የቤቶች ግንባታ ማህበር ሥራዎች የሚጸምበትን መዋቅርና አደረጃጃት በማጥናትይዘረጋል፤ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ያስተካክላል፤

(ሠ) የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ቅንጅትና ትስስር በመፍጠር ለመኖሪያ ቤት ግንባታ የመሥረተልማት አቅርቦትና ግብዓቶች እንዲሟሉ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤ ሁኔታዎችንያመቻቻል፤

(ረ)የመኖርያ ቤት ግንባታ ማህበር አደረጃጀትና ምዝገባ ላይ ያለዉን አፈጻጸምና ቅሬታ ይከታተላል፤ያስተካክላል፤

2) የኢንዱስትሪናከተሜልማትጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

በሌሎች ህጎች የተሠጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆነ ው፣ ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡ -

(ሀ) በኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጽህፈት ቤት የቤቶች ጉዳይን የሚከታተል መዋቅር በማዘጋጃቤትና በታዳጊ ማዘጋጀ ቤት ከተሞች ወስጥ የወረዳ መዋቅር በሌለበት ቦታ የመኖሪያ ቤትማህበር ያደራጃል፤ ይመዝግባል፤ የሕግ ሰውነት ይሰጣል፤

(ለ) የመማስረቻ ሞዴል፣ ቃለ ጉባኤ፣ የመተደደሪያ ደንብ ሞዴል እንዲሁም ከቢሮ የሚከለትን የተለላያዩ ሰነዶችን ለከተሞች ያስተላልፋል፤

(ሐ) በዞን በኩል ለሚደራጁ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ማህበራትየህጋዊ ሰውነት የምሥክር ወረቀትይሰጣል፤

(መ) የማህበሩ አባል በተለያዩ ምክንያቶች ከለቀቀ ወይም ከአባልነት ሲሠረዝ ጉዳዩን በማጣራትያረጋግጣል፤

(ሠ) በጽህፈት ቤት በኩል የሚነቡ ቤቶች ሲጠናቀቁ ለተመዝገቡ አባላት መድረሣቸውን ከጽህፈት ቤቱ ጋር በመሆን ያረጋግጣል፤

(ረ) በመደራጀት የተመዘገቡ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ማህበራት ሥራ ሲጀምሩ ወጪና ገቢያቸውን አስመልክቶ ሒሣባቸውን በትክክል መዝግበው እንዲይዙ ይከታተላል፤ አስፈላጊ ሲሆንም ሒሣባቸውን ፍቃድ ባለው ኦዲተር አስመርምሮ ሪፖርቱ እንዲቀርብ ያደርጋል፤

(ሰ) ተደራጅቶ የነበረው የመኖሪያ ቤት ግንባታ ማህበር በተለያየ ምክንያት ከፈረሰ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ በኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ፣ ወይም በኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ማህበር ዝግ ሒሣብ ወስጥ ተይዞ ያለው ገንዘብ ለአባላት እንዲመለስ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተወስኖ በቃለ ጉባኤ ተይዞ ጥያቄ ሲቀርብ በህግ መሰረት መሆኑን አጣርቶ ውሳኔ ይሠጣል፤

(ሸ) በህብረት ሥራ ማህበራት ህጎች ላይ የተደነገጉ ሌሎች የተለያዩ ሥራዎችና ሃላፊነቶችን ይፈፅማል፡፡

3) የከተማ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባራት

በሌሎች ሕጎች የተሠጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማ መስተዳድሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

(ሀ) በማዘጋጃ ቤት ከተሞች መስተዳደር የቤቶች ጉዳይ ለማስፈፀም በተዋቀረው ሥራ ሒደት የቤቶች ግንባታ ማህበርን በማደራጀትና በመመዝገብ ሕጋዊ ሰውነት ይሰጣሉ፤

(ለ) በማህበር የሚደራጅ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ ወስጥ የተደነገጉትን የመስፈርቶች መረጃ አሟልቶ መቅረቡን ያጣራል፤ ያረጋግጣል፤

(ሐ) የቤት ግንባታ ማህበር አስፈላጊነት፣ የመደራጀትና የምዝገባ ሥርዓትና ሒደትን አስመልክቶ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሁሉ ግልፅነት ባለው ሁኔታ በማዘጋጀት ይሰጣል፤

(መ) አባላት የሚመዘገቡበት ሁኔታ የተለያዩ ቅፆች፣ የመመስረቻ ፅሑፍ ቃለ ጉባኤ፤ የመተዳደሪያ ደንብ ሞዴል፤ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ከቢሮ በሚላከለት ሞዴል ላይ በመመስረት ስራ ላይ ያወላል፤

(ሠ) አባሉ በተለያየ ምክንያት ማህበሩን ከለቀቀ ወይም ከአባልነት ከተሠረዘ ጉዳዩን በማጣራት ያረጋግጣል፤

(ረ) በማሰሪያ ቤቶች በኩል የሚገነቡ ቤቶች ሲጠናቀቁ ለተመዘገቡት አባላት መድረሱን ከማስሪያ ቤቱ ጋር በመሆን ያረጋግጣል፤

(ሰ) ተደራጅተው የተመዘገቡ ማህበራት ሥራ ሲጀምሩ ወጪና ገቢያቸውን በተመለከተ ሒሣባቸውን በትክክል መዝግበው እንዲይዙ ይከታተላል፤ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜም ሒሰባቸውን ፍቃድ ባለው ኦዲተር አስመርምሮ ሪፖርቱ እንዲቀርብ ያደርጋል፤

(ሸ) ተደራጅተው የነበሩ ማህበራት በተለያየ ምክንያት ሲፈረሱ በዝግ የባንክ ሒሣብ ወስጥ ተቀምጦ ያለው ገንዘብ ለአባላት እንዲመለስ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተወስኖ በቃለ ጉባኤ ተይዞ ጥያቄ ሲቀርብ ገንዘቡ እንዲለቀቅላቸው ያደርጋል፤

(ቀ) በህብረት ሥራ ማህበር ህጎች ላይ የተደነገጉ ሌሎች የተለያዩ ሥራዎችና ሀላፊነቶችን ይፈጽማል፡፡

4) የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

በሌሎች ህጎች የተሠጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

(ሀ) ለማህበራት የመኖሪያ ቤት ግንባታ የሚውለውን መሬት ያዘጋጃል፤ ያስወስናል፤ ሲፈቀድ ለማህበራት በምዝገባቸው ቅደም ተከተል መሰረት ይሰጣል፤

(ለ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት ተወስኖ የተዘጋጀወን ሜት በአስር የሥራ ቀናትወስጥ የሜት ይዞታ ሰነድ አዘጋጅቶ በማስረከብ ላደራጀው አካል ያሣወቃል፤

(ሐ) ለማህበሩ የሚሰጠው ሜት በሊዝ በሚተዳደሩ ከተሞች ወስጥ በሊዝ መነሻ ዋጋ፤ በኪራይ በሚተዳደሩ ከተሞች ወስጥ በኪራይ መነሻ ዋጋ ይሰጣል፤

(መ) የተዘጋጀው ሜት ማስፈርቱን አሟልተው ለቀረቡት ማህበራት ብዛት የማይዳረስ ከሆነ ሜቱን በማህበራቱ ምዝገባ ቅደም ተከተል መሰረት ይሰጣል፤

(ሠ) ለማህበር የሚሰጥ ሜት በከተማው ፕላን መሰረት ለመኖሪያ ቤት ተስማሚ ቦታ መሆንአለበት፤

(ረ) የማህበራቱ የመኖሪያ ቤት ግንባታ በተፈቀደው ፕላን መሰረት ተገንብቶ ማጠናቀቁን በዞኑወይም በከተማው የኮንስትራክሽን ጽህፈት ቤት ሲረጋገጥ በማህበሩ ስምያለወን የባለቤትነት ማስረጃ በያንዳንዱ አባል ስም አዘጋጅቶ ይሰጣል፤

(ሰ) ሜት የተሰጣቸው ማህበራት ማስረጃን አቀናጅቶ ይይዛል፡፡

## 5) የዞንናየከተማኮንስትራክሽንጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

(ሀ) ሜት የተፈቀደላቸው የቤቶች ግንባታ ማህበራት በከተማው ፕላን መሰረት የግንባታደረጃወን በማጠበቅ እንዲገነቡ የፕላን ስምምነት ማስረጃ ይሰጣል፤

(ለ) የፕላን ስምምነት የተሰጣቸው የቤቶች ግንባታ ማህበራት የከተማ ልማት ፕላንመዋቅር እንዲሁም የግንባታው ደረጃ በሚፈልገው መሰኩ ህጋዊ ዲዛይን አሟልቶ ከቀረበ የግንባታ ፍቃድ ይሰጣል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ያስተካክላል፤

(ሐ) ማህበራት የግንባታ ማሻሻያና ዕድሳት ጥያቄ ካቀረቡ በመመርመር ፍቃድ ይሰጣል፤

(መ) የቤቶች ግንባታ ፍቃድ የተሰጣቸው ማህበራት ማስረጃዎችን አቀናጅቶ ይይዛል፤

(ሠ) ማህበራቱ የደረሱበትን የቤቶች ግንባታ ደረጃ በማየት በዝግ የባንክ ሒሣብ ወስጥ ያለው ገንዘብ እንዲለቀቅላቸው ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ ይጽፋል፡፡

(ረ) ሜት የወሰዱና የግንባታ ፈቃድ ያገኙ ማህበራት በህንፃ አዋጅ መሰረት በገቡት ወልመሰረት ግንባታ መጀመራቸወንና መጨረሳቸወን ይቆጣጠራል፤

(ሰ) የማህበራት ቤት በወሉ መሠረት ማለቁን በሚረጋገጥ ካርታና ፕላን ለማህበሩ አባላትበግል ተሠርቶ እንዲሰጣቸው ለኤጀንሲወደብዳቤይጽፋል፡፡

(ሸ) የቤቱ ግንባታ በተቀማጠለት ስታንደርድና ዲዛይን ላይ በመመሥረት ማለቁን ያረጋግጣል፤ ርክክብ እንዲደረግ ለማህበሩ ደብዳቤ ይጽፋል፤

## 6) ሠራተኞቻቸው በማህበር የተደራጁ ማሣሪያ ቤቶችየስራ ድርሻ

(ሀ) ሠራተኞች ማስሪያ ቤታቸው በዚህ ደንብ ወስጥ የተደነገገወንየመደራጃ ማስፈርትያሟሉመሆናቸወን በማለየት ሁኔታን በማመቻቸት ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤

(ለ) ለሠራተኞቻቸው በማህበርየመኖሪያ ቤት የሚገነቡ ማሣሪያ ቤቶችየሰራተኞቹንስም ለቤቶች ግንባታየሚያስፈልወን ወጪ ያህል በባንክ ወይም በኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ማህበር በማስገባት ማህበሩን ለሚያደረጀው አካል ዘንድ በመቅረብ ማህበሩን ያስማዝግባል፤ ቤቱንለማንባት ወል ለፈፀመውአካል ያስታወቃል፤

4) ማንኛውም የማህበር አባል በማህበሩ ስም በተከፈተው ዝግ የባንክ አካወንት ቁጥር ገቢ ሚደረግ አለበት፤

5) ማንኛውም የማህበሩ አባላት፡ -

(ሀ) በሚከሄደው ስብሰባ ላይ የማ ኘት፣ የመወያየት፣ የማሪጥ ፣ የመጢጥ፣ አስፈላጊወሳኔን በጋራ የመወሰን፤

(ለ) የመተዳደሪያ ደንብ የማውጣት፣ የሚጸድቅ፣ በመማሢቻ ጸሁፍ ቃለ ጉባኤ እና ሌሎችላይ የሚፈረም፤

(ሐ)የመመዝገቢያ ክፍያ እና ድርሻ ወይም መዋጮ የመክፈል፤

(መ) የማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴና የሚከሄደወን የቤት ግንባታ በቅርበት በግንባታው ቦታበማ ኘት የመከታተልና የመቆጣጠር፤

(ረ)በጉልበትና በዕውቀት ለመደገፍ በግልም ይሁን በጋራሃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

(ሰ) የቤት ግንባታው ሲጠናቀቅ በግንባታውቦታ በማ ኘት በዕጣ የወጣውን ቤት መወሰድአለበት፡፡

**ክፍል ሰባት**

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 34.ክልከላ

በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ወስጥ ከተደነገጉት ማከፈርቶች ውጭ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ማህበር ሚደራጀትና መደራጀት የተከለከለ ነው፡፡

### 35.ቅጣት

ማንኛውም ሰዉ በዚህ  ደንብ ወስጥ ተደነገጉትን ጉዳዮች በመተላለፍ የተመዘገበ ወይም የማዝገበ፣ለመመዝገብ የሞከረ ወይም ያሳሳተ፣ የምዝገባን ሂደት ያወከ፣ የሐሰት ማስረጃ የሰጠ ወይም ያቀረበ በፍትሐብሄር ወይም በወንጀል ሕግ ወይም በሁለቱም የሚጠየቅ ይሆናል፡፡

### 36.የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት

1) የመደራጀት ወሳኔና የምዝገባ ሁኔታን አስመልክቶ በሚደራጅና በሚዝገብ አካል ላይ የሚቀርብ ቅሬታ በፅሁፍ በአስር ተከታታይ የስራ ቀናት ወስጥ ማህበሩን ላደራጀው አካል መቅረብ አለበት፡፡

2) ያደራጀው አካል በሰጠው ወሳኔ ላይ ያልረካ አካል ቅሬታውን በተለያየ ደረጃ እስከ ቢሮ ለሚገኙ የቅሬታ ሰሚ መዋቅር ማቅረብ ይቻላል፡፡ የሚሰጠዉም ወሳኔ የኦሮሚያ ክልልየአስተዳደራዊ ጉዳዮች አቤቱታና የህዝብ ቅሬታ ለማስተናገድ በወጣው ደንብ ማስረት በተወሰነ ጊዜ ወስጥ መሆን አለበት፡፡

### 37.ድጋፍ የማስጠት ግዴታ

ማንኛውም አካል ለዚህ ደንብ አፈፃፀም ድጋፍ የማስጠት ግዴታ አለበት፡፡

### 38.ተፈጻሚ ት የሚኖራቸው የሕጎች

1) የኦሮሚያ ክልል አስተዳደር የመኖሪያ ቤት ግንባታ የህብረት ሥራ ማህበር ለማደራጀት የወጣው መመሪያ ቁጥር 11/2007 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

2) ማንኛውም ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ደንብ፣ መመሪያና ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ ወስጥ በታቀፉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ት አይኖራቸውም፡፡

### 39.መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ይህንን ደንብ ለማስፈፀም ቢሮው መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

**40. ደንቡ ሥራ ላይ የሚውልበት ቀን**

ይህ ደንብ ከሚያዝያ 28/2008 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

**ሙክታር ከድር**

**የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዝዳንት**

**ፊንፊኔ**

**ሚያዝያ 28/2008 ዓ.ም.**